# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# የጠፋው ልጅ



**ጸሐፊው**: Edward Hughes
**ምሣሌ አቅራቢው**: Lazarus
**የተተረጎመው**: Abel Eshetu
**ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው)**: Ruth Klassen; Sarah S.

**ታሪክ** 45 **ከ** 60 **ዎቹ መሃከል**

**www.M1914.org**

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*

ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

**አማርኛ** Amharic



ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር ምህረት ለሰዎች ይናገር ነበር። የአይሁድ መሪዎች ግን ከኃጢአተኞች ጋር ወዳጅ ስለነበር ኢየሱስን ይነቅፉት ነበር።



የመጀመሪያው ታሪክ መቶ በጎች ስለነበሩት አንድ ሰው ነበር።



ከእነርሱም አንዲቷ ጠፋችበት።


ሰውዬው ወዲያው
ዘጠና ዘጠኙን ትቶ
አንዲቷን
ፍለጋ ሄደ።
3


እስኪያገኛትም ድረስ
በየቦታው ፈለጋት።
ሲያገኛትም ደስ
አለውና በትከሻው
ላይ ተሸክሟት ወደ
ቤቱ መጣ።
4


ከዚያም ለጎረቤቶቹ
“ከእኔ ጋር ደስ
ይበላችሁ። የጠፋችብኝን
በግ አግኝቻታለሁ”
አላቸው።
5


ኢየሱስም ንስሐ
በሚገባ በአንድ ሰው
በመንግስተ ሰማያት
ታላቅ ደስታ ይሆናል
አላቸው። ንስሐ ማለት
በኃጢአታችን በማዘን
ኃጢአትን ለመተው
ፈቃደኛ መሆን
ማለት ነው።
6


ኢየሱስ የነገራቸው
ሁለተኛው ታሪክ ደግሞ
አስር ድሪም (የብር
ሳንቲሞች) ስለነበራት
ሴት ነበር። ብዙ ጊዜ
ቆጥባ ያጠራቀመችው
ሊሆን ይችላል።
ያሳዝናል! አንዲቷ
ድሪም ጠፋችባት።
7


የጠፋባትን እስክታገኝ ድረስ
ቤቷን ጠረገችው፣በረበረችው።
8


ባገኝችውም ጊዜ ጐረቤቶችዋን ሁሉ ጠርታ የጠፋውን ድሪሜን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ አለቻቸው።
9
ኢየሱስም ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።
10
ኢየሱስ የነገራቸው ሶስተኛው ታሪክ በጣም ያሳዝናል። የአባቱን ቤት ትቶ ስለጠፋው ልጅ ነበር።
11
ልጁም ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፥ ከዚያም እያባከነ ገንዘቡን በተነ። ከዚያም በአገሩ ረሀብ ስለገባ በምግብ እጦት ይጨነቅ ጀመር።
12
ከረሀቡም የተነሳ የአሳማ እረኛ ሆነ። አሳማዎችም ከሚበሉት ምግብ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፥ የሚሰጠውም አልነበረም።
13
ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ፡ እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ አሽከሮች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ።
14

“ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና። አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ። ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም። ከአሽከሮችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ” አለ።



15

ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ። እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፥ አባቱም ወደ ልጁ ሮጦ አንገቱን አቀፈውና ሳመው።



16

ልጁም። አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም አለው። አባቱ ግን አሽከሮቹን አለ። ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፥ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ፤



17

ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና አሁን ሕያው ነው፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር። እግዚአብሔር በንስሐ ወደ እርሱ የሚመለሱትን ይወዳቸዋል።



18

የጠፋው ልጅ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሉቃስ ምዕ. 15

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣ ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16